Oslo

**ሚስጢር መጠበቅ**
የሙያ አማካሪው ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት። ይህ ማለት የሙያ አማካሪው በንግግራችሁ ውስጥ ስለ ተናገሩት ለማንም ሰው መናገር አይችልም ማለት ነው።

**አስተርጓሚ**
በኦስሎ የሙያ ምክር ቢሮ፣ በሙያ ምክር ለመተርጎም ብቁ የሆኑ አስተርጓሚዎችን እንጠቀማለን።

**የሙያ ኣማካሪ ማስታወሻ**
የሙያ ምክክሩ ሲጠናቀቅ፣ የሙያ ኣማካሪው ስለ ፍላጎትዎ እና በኖርዌይ ውስጥ ስላልዎት የትምህርትና የስራ እድሎች በሚመለከት በውይይትዎ ውስጥ የተናገሩትን ሓሳብ በማስታወሻው ይጽፋል። በNAV ውስጥ ከርስዎ ጋ ግንኙነት ያለው ሰውም ማስታወሻውን ያነባል። ከዚያም NAV ስለ ፍላጎትዎ እና እቅዶችዎ ጠቃሚ መረጃ ያገኛል፣ ይህም ለመግቢያ ፕሮግራምዎ አስፈላጊ ነው።

**የውህደት እቅድ**
እርስዎ፣ NAV እና በአገልግሎት ማእከል የሚገኘው የኖርዌጂያን አማካሪ የመጀመሪያውን የውህደት እቅድዎ ለመፃፍ ከሙያ ምክክሩ በኋላ ይገናኛሉ።

Oslo

# Velkommen!

**Adresse:**
Karoline Kristiansens vei 8
0661 Oslo

**Telefon:**
23470000

**Epost:**
karriereveiledning.intro.felles
@osloskolen.no

**Post:**
Oslo Kommune,
Utdanningsetaten,
Oslo Voksenopplæring
Servicesenter,
Postboks 6127 Etterstad
0602 Oslo



Oslo

# የመጀመርያው የሙያ ምክር

# የመጀመርያው የሙያ ምክር

የሙያ ምክር ሊረዳዎት እንዲሁም ስለ ትምህርት እና ስራ ጥሩ ምርጫዎችን ለማድረግ የበለጠ በራስ መተማመን እንዲኖርዎት ሊያግዝዎት ይችላል። በኦስሎ የሙያ ምክር ቢሮ፣ ምን ማድረግ እንደሚችሉ እና ምን እንደሚፈልጉ የሚያነጋግርዎት የሙያ አማካሪ ያገኛሉ። የሙያ አማካሪው በህይወትዎ ቀደም ብለው ስለ ሰሩት የስራ ዓይነትና ያለዎትን ልምድ በኖርዌይ ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ያነጋግርዎታል። እኛ እርስዎን በደንብ



Oslo

**ማሰላሰል**

በኦስሎ የሙያ ምክር ቢሮ ከዚህ ቀደም ስላደረጉት ነገር፣ ስለፍላጎቶችዎ፣ ማን እንደሆኑ እና በኖርዌይ ውስጥ ከስራ እና ትምህርት በተያያዘ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ የሚያነጋግርዎትን የሙያ አማካሪ ያገኛሉ።

**የኋላ ታሪክዎ**

በኖርዌይ ውስጥ በአዲሱ ህይወትዎ ውስጥ ጠቃሚ የሚሆን ከዚህ በፊት ያዳበሩት እውቀት እና ልምድ ያለዎት ይመስለናል። ስለዚህ፣ በአገርዎ ስለነበርዎት ሕይወት እንደሚነግሩንም ተስፋ እናደርጋለን።

**ራስዎ ይወስናሉ**

እርስዎ እና የሙያ አማካሪው በሙያ ምክክር ግዜ ስለምንድን እንደምትነጋገሩ ስምምነት ያደርጋሉ። ስለ ወደፊት ህይወትዎ ምርጫ የሚመርጡት እርስዎ ነዎት፣ የሙያ አማካሪውም እርስዎ ምን ማድረግ ወይም መምረጥ እንዳለብዎ አይወስንም፣ ነገር ግን በአንድ ላይ ሆናችሁ ስላለዎት ዕድሎች ይነጋገራሉ።

Oslo

## የመጀመርያው የሙያ ምክር በኦስሎ

በኦስሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በኦስሎ የአዋቂዎች ትምህርት አገልግሎት ማእከል በርካታ ስብሰባዎች ይኖርሃል፡-

1. የጥናት ስብሰባ
2. የሙያ ምክር
3. የውህደት እቅድ ስብሰባ

እነዚህ ስብሰባዎች የተያያዙ ናቸው፣ በሁሉም ስብሰባዎች ላይ መገኘትዎም አስፈላጊ ነው።

